PRAIRIE MIDDLE SCHOOL

# የተማሪ መመሪያ መጽሐፍ

## የ2024-2025 የትምህርት ዘመን

# የቋንቋ ትርጉም እገዛ?

ዲስትሪክቱ ለወላጆች እና ቤተሰቦች በጥያቄ መሰረት የቋንቋ እርዳታ አገልግሎቶች አሉት። አገልግሎቶችን ለመጠየቅ፣ እባክዎን የት/ቤትዎን ርእሰመምህር ያግኙ ወይም ለትርጉም ቢሮ ድጋፍ በዝህ ስልክ ይደዉሉ 720-554-5046

## የPRAIRIE መካከለኛ ትምህርት ቤት
## የትምህርት ቀን

የትምህርት ቀናችን በ8:50 ሰአት ይጀምራል እና በ3:45 ፒ.ኤም ያበቃል። ቁርስ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ህንፃው በ8:00 ሰአት ይከፈታል።. ለቁርስ፣ ተማሪዎች በእረፍት በሮች በኩል እንዲገቡ ይጠበቅባቸዋል። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ተማሪዎችን በበቂ ሁኔታ የሚቆጣጠሩት አነስተኛ ሰራተኞች ሰላሉ ተማሪዎች ከጠዋቱ 8:00 ሰዓት በፊት በህንፃው ውስጥ መጠበቅ አይችሉም 8:40 ላይ የአካዳሚክ አዳራሽ ይከፈታል። ከጠዋቱ 9:00 ሰዓት በኋላ በሮቹ ይቆለፋሉ፣ እና ተማሪዎች ከትምህርት ቤቱ በስተ ምዕራብ ባለው ዋና መግቢያ ወደ ህንጻው መግባት አለባቸው።

### የትምህርት ቤት መዘጋት/ዘግይቶ መጀመር

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት የትምህርት ቤቱን መዘጋት እና መዘግየት መረጃ በኮኔክቴድ፣ በዋና ዋና የቴሌቭዥን ኔትወርኮች እና በሬዲዮ ጣቢያዎች እንዲሁም በዲስትሪክታችን እና በትምህርት ቤታችን ድረ-ገጾች ያስተላልፋል። (www.cherrycreekschools.org).ትምህርት ቤት ሲዘጋ ሁሉም ከትምህርት በኋላ እና የማታ እንቅስቃሴዎችለሌላ ጊዜ ይተላላፋሉ ወይም ይሰረዛሉ። ትምህርት ቤት ዘግይቶ በምጀመርበት ቀናት ፣ የጠዋት አውቶቡሶች ከወትሮው 1 ½ ሰዓት ያህል ዘግይተው ይመጣሉ።በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ፣ተማሪዎችን ወደ/ከ ስፖርት እና የተለያዩ እንቅስቃሴዎች የሚያመላልስ አውቶቡሶች ሊሰረዙ ይችላሉ። ቤተሰቦች ለእንደዚህ አይነት ድንገተኛ ሁኔታዎች እቅድ እንዲኖራቸው ይመከራል.

### ማስታወቂያዎች

እንደ የትምህርት ቤት ካላንደር፣ መጪ ክስተቶች፣ የምሳ የምግብ ዝርዝር እና ሌሎች መረጃዎች ያሉ አጠቃላይ መረጃዎች በድረ-ገጻችን ላይ ይለጠፋሉ።www.cherrycreekschools.org/prairie. ለለታዊ የተማሪ ማስታወቂያዎች በትምህርት ቀን ላይ ይነገራሉ።እንዲሁም በህንፃው ውስጥ በተቀመጡ ሞንተሮችም ላይ ይታያሉ።

### ጎብኝዎች እና አቅራቢዎች

**መልዕክቶች እና ዕቃ አድረሽዎች**

ተማሪው እቃውን እቤት ውስጥ ትቶ በወላጅ ወደ ትምህርት ቤት ከደረሰ፣ ከጥበቃው ቢሮ እነዚህን እቃዎች መውሰድ የተማሪው ሃላፊነት ነው።

**የምሳ አምጭዎች**

በደህንነት ስጋቶች ምክንያት የምግብ አቅርቦት አገልግሎቶች (ዶርዳሽ፣ ግሩብሃብ፣ ወዘተ) አይፈቀዱም። ወላጆች በተማሪው የምሳ ሰአት በዋናው የመግቢያ የጥበቃ ቢሮ ለተማሪዎቻቸው ምግብ እንዲያመጡ ይፈቀድላቸዋል። ምግብ ከተማሪው ምሳ ሰአት በኋላ በወላጅ የሚቀርብ ከሆነ እስከ የትምህርት ቀን መጨረሻ ድረስ በሲኩሪቲ ቢሮ ውስጥ ይቆያል።

**ጎብኝዎች**

.ወላጆች የትምህርት ቤት ሕንፃዉን እና የመማሪያ ክፍሎችን እንዲጎበኙ ይፈቀድላቸዋል እንደዝሁም ይበረታታሉ።እባክዎን ከልጅዎ መምህር እና ዲኑ ጋር አስቀድመው ያዘጋጁ። ጎብኚዎች በምእራብ መግቢያ በኩል በባንዲራ ምሰሶ በኩል መግባት አለባቸው። እንደደረሱ ሁሉም ጎብኚዎች በጥበቃ ቢሮ ውስጥ የፎቶ መታወቂያ ማቅረብ አለባቸው። ጎብኚዎች በኔትወርክ በተገናኘ ብሔራዊ ዳታቤዝ ይቃኛሉ ከዚያም ለጉብኝቱ ጊዜ የሚያረጋትን የጎብኚ ባጅ ያገኛሉ። እባክዎ የክፍል ጉብኝቶች ከአስተማሪዎች ጋር ስብሰባ ለማድረግ የታሰቡ እንዳልሆኑ ያስታውሱ። በማንኛውም ጊዜ ወላጆች ከአስተማሪ ጋር ቀጠሮ መያዝ ይችላሉ

<u>በትምህርት ቀን ሌሎች የተማሪ ጎብኚዎች (ወንድሞች/እህቶች ፣ ዘመዶች፣ ጓደኞች፣ ወዘተ) እንዲጎበኙ ወይም ምልከታ አይፈቀድላቸውም። ተማሪዎች ከሚጎበኟቸው መምህር ቀድመው ፈቃድ እስካላገኙ ድረስ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጉብኝት አይፈቀድም እና ጉብኝቶች ከትምህርት ሰዓት በኋላ</u> መከሰት አለባቸው

## የአካዳሚክ መረጃዎች

**የትምህርት ውጤቶች እና አሰጣጥ**

ውጤቶች የሚገለጹት በPowerSchool ስርዓት ነው። ዉጤቶች የሚወሰኑት በሚከተለው መለኪያ በመጠቀም ነው፡

| | |
|---|---|
| A = 90-100% | F = 59% እና በታች |
| B = 80-89% | I = አልተጠናቀቀም |
| C = 70-79% | S = በቂ |
| D = 60-69% | U = በቂ ያልሆነ |

**የተማሪ የዉጤት ካርድ**

የፕራይሪ መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አመት በሁለት ሴሚስተር ላይ የተመሰረተ ነው፣ እያንዳንዱ ሴሚስተር ሁለት ሩብ ያቀፈ ነው። እያንዳንዱ ሩብ (በዓመት አራት) የሪፖርት ካርዶች በPowerSchool በ my.cherrycreekschools.org በኩል ይገኛሉ እና የመጨረሻ የዉጤት ቀን ለወላጆች ይነገራል። ወላጆች ወቅታዊዉን የተማሪዎችን ዉጤት ለማወቅ በተደጋጋሚ PowerSchoolን እንዲመለከቱ ይበረታታሉ። ሁሉም የሪፖርት ካርዶች በኤሌክትሮኒክ መንገድ ብቻ ይገኛሉ።

**የተማሪ እውቅና/ሽልማት**

የተማሪዎችን ስኬት በተለያዩ መንገዶች እናከብራለን። ተማሪዎች ለከፍተኛ ዉጤት (የክፍል ነጥብ አማካኝ 3.5 ወይም ከዚያ በላይ)፣ የአካዳሚክ ዕድገት (GPA ጭማሪ)፣ በመልካም ጸባይ ፣ የወሩ ተማሪ፣ እና በእንቅስቃሴዎች እና አትሌቲክስ ተሳትፎ እውቅና ያገኛሉ።

**የየቤት ስራ እና የትምህርት ድጋፍ**

የቤት ስራ የመማር ሂደት አስፈላጊ ማራዘሚያ ነው። የሚጠናቀቀው ራሱን ችሎ፣ ከክፍል ውጪ ነው፣ እና በአስተማሪው ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር አይደለም። መምህራን ለተማሪዎቻችን አካዴሚያዊ እድገት ጠቃሚ እና ትርጉም ያለው የቤት ስራን ለመስጠት ቃል ገብተዋል። ይህንን በአእምሯችን ይዘን፣ ተማሪዎች ሁሉንም ስራዎች እንዲያጠናቅቁ እንጠብቃለን። ይህ ለአካዳሚክ እድገት ብቻ ሳይሆን ከመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባሻገር ለስኬት አስፈላጊ የሆኑትን ጠቃሚ የአካዳሚክ ባህሪያትንም ይረዳል። የአንድ ሰዓት የቤት ስራ ለመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች የተለመደ ነው ተብሎ ይታሰባል።.

PMS ለሁሉም ተማሪዎች የአካዳሚክ ድጋፍ አለ። መምህራን ለተወሰኑ ጊዜያት ወይም በቀጠሮ ለተማሪዎች ድጋፍ ይሰጣሉ። አንድ ተማሪ ትምህርቱን ለመረዳት፣ የጎደሉትን ሥራዎችን ለመሥራት ወይም ፈተና ለመፈተን ተጨማሪ እገዛ የሚያስፈልገው ከሆነ ከመምህሩ ጋር መነጋገር እና የተወሰነ ጊዜ መመደብ አለበት። የአካዳሚክ ድጋፍ ከትምህርት በኋላ በቤተ-መጽሐፍት ውስጥም ይገኛል።

**የአካዳሚክ ቴክኖሎጂ**

PowerSchool እና Schoology በተማሪዎች አካዴሚያዊ ስኬት ውስጥ ጠቃሚ መሳሪያዎች የሆኑ ሁለት ድረገጽ ላይ የተመሰረቱ ፕሮግራሞች ናቸው። ተማሪዎች እና ወላጆች ለእያንዳንዳቸው የተጠቃሚ መታወቂያ እና የመግቢያ መረጃ ይሰጧቸዋል ። ጣቢያዎች በወላጅ ፖርታል በኩል መገኘት ይችላሉ። **<u>https://my.cherrycreekschools.org</u>**.

የተማሪዎችን ውጤት ለመጠበቅ እና ለአቴንዳንስ ጥቅም ላይ ይውላል እና በየሳምንቱ በአስተማሪዎች ይሻሻላል. የትልልቅ የቤት ስራዎችን አርሞ ለመጨረስ እና ፣ ውጤትን ወደ PowerSchool ለማስገባት መምህራንን በርካታ ቀናትን ሊወስድ ይችላል።<u>. የPowerSchool የወላጅ ፖርታል የውጤት ሂደት ሪፖርቶችን ለወላጆች በመደበኛነት በኢ-ሜል እንዲላክ ለመመዝገብ አማራጭ ይሰጣል</u>። PowerSchoolን በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎት፣እባክዎ እርዳታ ለማግኘት 720-747-3122 ይደውሉ።

ስኮሎጂ ብዙ መምህራኖቻችን የሚጠቀሙበት የክፍል ቅጥያ ነው። ወቅታዊ የክፍል የቀን መቁጠሪያዎች፣ የኮርስ መረጃ፣ ምደባዎች እና ተጨማሪ ማግኘት ይችላሉ።

### የአቴንዳንስ መመሪያ

የኮሎራዶ ስቴት ህግ ሁሉም ተማሪዎች እስከ 17 ዓመታቸው ድረስ በትምህርት ቤት እንዲማሩ ያዛል። የቼሪ ክሪክ ዲስትሪክት ካለንደር አራት

የዕረፍት ጊዜዎችን ያቀርባል፡ የፎል ዕረፍት፣ የታንክስጊቪንግ ዕረፍት፣ የሠመር ዕረፍት እና የስፕሪንግ ዕረፍት። እባካችሁ ወላጆች የእረፍት ጊዜያቸውን ከእነዚህ ጊዜያት ጋር እንዲያመቻቹ እንጠይቃለን።
ይቅርታ የሚደረግለት ቀሪ ድግግሞሽ ከመጠን በላይ ከሆነ፣ ተማሪዎች ለአተንዳንስ ጣልቃገብነት ወደ ዲኑ ሊመሩ ይችላሉ። ቅጣቶች የአቴንዳንስ ውልን፣ የሚፈለጉ የህክምና ሰበቦችን፣ ወደ ዲስትሪክት የተማሪ አቴንዳንስ ግምገማ ቦርድ መላክ እና በመጨረሻም ፍርድ ቤትን ሊያካትቱ ይችላሉ።. ስለሆነም፣ ተማሪዎች እና ወላጆቻቸው በዓመት ለእያንዳንዱ ተማሪ በህግ የሚጠየቁትን 1056 ሰአታት (በግምት 176 ቀናት) የትምህርት ቤት ክትትልን ሀላፊነት ለመቀበል እንዲረዱን እንጠይቃለን።

**የአቴንደንስ ስልክ መስመር**

አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት ሲቀር ወላጅ/አሳዳጊ ከጠዋቱ 10፡00 ሰዓት በፊት በዝህ ቁጥር ላይ 720-747-3010 መደወል አለበት።.እነዚህ ጥሪዎች በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ብቻ ሊደረጉ ይችላሉ። የሚከተለው መረጃ መሰጠት አለበት፡ ቀን፣ የደወለው ሰው ስም እና ከተማሪው ጋር ያለው ግንኙነት፣ የተማሪው ስም፣ የክፍል ደረጃ ፣ የመቅረት ወይም መዘግየት ምክንያት፣ እና ለስንት ቀን ቀሪ እንደምሆኑ ፣ የሚታወቅ ከሆነ። እባክዎ የተማሪውን የመጀመሪያ እና የአያት ስም ይጥቀሱ ።

ተማሪዎ ከትምህርት ቤት ቀሪ በሚሆንበት ቀን ወይንም ካላቋረጠ/ች እና ወላጅ ከልደወለ በኮኔክቴድ ኢድ በኩል የስልክ መልእክት ማሳወቂያ ይደርስዎታል እና ቀሪው እንደ ያለምክንያት ቀሪ ይመዘገባል :; የፕራይሪ መለስተኛ ደረጃ ት/ቤት "Talking Points" የሚባለዉን የአጭር ጹሁፍ መተግበሪያንም ይጠቀማል። ይህንን በስልክዎ የመተግበሪያ መደብር ውስጥ ማውረድ እና ለ Prairie Middle School መመዝገብ ይችላሉ።l. ይህ መተግበሪያ ከልጅዎ አስተማሪ ጋር እንዲገናኙ ያስችልዎታል
<u>ሙሉ ቀን ቀሪ የሆኑ ተማሪዎች በዚያ ቀን ከትምህርት በኋላ በአትሌቲክስ/እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ብቁ አይደሉም</u>

**ቀጠሮዎች/ቀድሞ የታቀደ መቅረት**

አንድ ተማሪ ቀደም ብሎ ከትምህርት ቤት መልቀቅ ካለበት፣ ተማሪው በወላጅ የተፈረመ ማስታወሻ ወደ አቴንዳንስ ቢሮ ማምጣት አለበት። ተማሪው በተገቢው ጊዜ ክፍሉን ለቆ ለመውጣት እና ወላጁን በአቴንዳንስ ቢሮ ለማግኘት ማለፊያ ይሰጠዋል ። አንድ ተማሪ ቀሪ እንደሚሆን/ትሆን አስቀድሞ ሲታወቅ ወላጆች አስቀድመው ማስፈቀድ ይችላሉ።. የዚህ ዓይነቱ ቀሪ ከመጠየቁ ቢያንስ ከሁለት ቀናት በፊት በስልክ ወይም በጽሑፍ ለአቴንዳንስ ቢሮ መቅረብ አለበት።

**ይቅርታ የተደረጋለቸው ቀሪዎች**

በ CCSD የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JH መሰረት፣ ተማሪዎች ከትምህረት ቤት ቀሪ በሚሆንበት ጊዜ ቀሪዉን የምያጸድቅ ትምህርት ቤቱ ነው ፣ እሱም እንደሚከተለው ይገለጻል።

- ጊዜያዊ ሕመም ወይም ጉዳት. ብዙ እንደዚህ ያሉ ቀሪዎች ካሉ ትምህርት ቤቱ የዶክተር ማስታወሻ ሊጠይቅ ይችላል።
- በአካል፣ አእምሯዊ ወይም ስሜታዊ እክል ምክንያት ረዘም ላለ ጊዜ ቀሪ መሆን
- ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል አከባበር ቀናት
- የቅርብ የቤተሰብ አባል ሞት
- የግዴታ የፍርድ ቤት ቀጠሮ
- ተቀባይነት ያለው ትምህርት ቤት ስፖንሰር የተደረገ እንቅስቃሴን በሚከታተሉበት ወቅት ቀሪ መሆን
- በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ጥያቄ በአስተዳዳሪው ቀድሞ የተፈቀደላቸው ቀሪዎች

**ያለምክንያት/ያለፍቃድ መቅረት/አቋራጭ**

. በቀደመው ዝርዝር ውስጥ ያልተገለጹት ሁሉም ቀሪዎች እንደ ያለምክንያት ቀሪዎች ይቆጠራሉ። እንደ ከመጠን በላይ መተኛት ወይም ከመጠን በላይ ቀሪዎች እንደ ይቅርታ የማይደረግላቸው ቀሪዎች ነቸው. ያለ ፈቃድ ከክፍል ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ግቢ የሚቀሩ ተማሪዎች እንደ አቋራጭ ይቆጠራሉ እና የዲሲፕሊን እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

**የማርፈድ ፖሊሲ**

አስፈላጊውን ትምህርት ለመቀበል ተማሪዎች ሁሉንም የትምህርት አይነቱን በሰዓቱ መከታተል አለባቸው ። ማርፈድ የመማር ሂደቱን ያበላሻል እና የተማሪዎችን የመማር እድል ያስተጓጉላል። አርፋጅ ተማሪዎች ትምህርት ቤት እንደደረሱ በሴኩሪቲ ቢሮ መመዝገብ አለባቸው። ይህ ዘግይቶ በሚመጣ አውቶቡስ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

- 1ኛ ማርፈድ - በክፍል መምህር ማስጠንቀቂያ ይሰጣል
- በ5ተኛው ማርፈድ ላይ ተማሪዎች እንደ ቅጣት በምሳ ሰአት ምሳቸውን በቢሮ ዉስጥ ይመገባሉ።
- ከመጠን በላይ ማርፈድ የአቴንዳንስ ዉል ዉጤትን ለመዳሰስ የወላጆችን ትብብር የሚጠይቅ ስብሰባ እንድጠራ ያደርጋል

**ቀሪዎች**

ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ቀሪ በሚሆኑበት ጊዜ ያመለጣቸዉን ሥራ መስራት /ማካካስ አስፈላጊ ነው። ተማሪዎች ከትምህርት ስቀሩ ለተሰጡ የቤት ስራዎች፣ ማስታወሻዎች ወይም አስፈላጊ መረጃዎች PowerSchool እና Schoology ማረጋገጥ አለባቸው። ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲመለሱ ለማካካሻ ሥራ መምህራኖቻቸውን ማነጋገር አለባቸው። ተማሪዎች ያመለጠቸዉን ሥራ ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በኋላ ለማካካስ ከፈለጉ፣ ከመምህራኖቻቸው ጋር ማመቻቸት አለባቸው።. . እባክዎ የልጅዎን አስተማሪዎች ያነጋግሩ፣ ያመለጡ ስራዎችን በስኩሎጂ እና PowerSchool ዉስጥ ይመልከቱ።

**የCCSD የተማሪ ባህሪ ፖሊሲዎች**

**የተማሪ ባህሪ (CCSD ፖሊሲ JIC**

ተማሪዎች በክልል ህጎች የተደነገገውን የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት የስነምግባር ህግን ማወቅ እና መከተል ይጠበቅባቸዋል.። እነዚህን ፖሊሲዎች መጣስ በቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት፣ በግዛት ህግ እና በትምህርት ቤት ህንጻ ፖሊሲ የተመሰረቱ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን እና መዘዞችን ያስከትላል።.ደንቦች እና መመሪያዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ሁሉንም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ንብረቶችን ጨምሮ እንዲሁም በት/ቤት የሚደገፉ እንቅስቃሴዎችን ይመለከታል ። እዚህ ያሉት ሁሉም መረጃዎች የዲስትሪክት ፖሊሲ አጭር ማጠቃለያ ነው።

የማንኛውም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ፖሊሲ እና/ወይም ደንብ ሙሉ ጽሁፍ ከትምህርት ቤቱ ወይም ከዲስትሪክቱ አስተዳደር ቢሮ በ 4700 S. Yosemite Street, Greenwood Village, CO 80111 ከተጠየቀ መቅረብ ይቻላል ፡ በተጨማሪም፣ ሁሉም የዲስትሪክት ፖሊሲዎች በሚከተለው በሚገኘው የቼሪ ክሪክ ትምህርት ዲስትሪክት ድህረ ገጽ በኩል ሊገኙ ይችላሉ።
**http://www.cherrycreekschools.org/StudentConduct**

**ድሲፕሊን እና ቅጣቶች**

የተማሪው ባህሪ ከሚጠበቀው ጋር የሚቃረን ከሆነ ወይም ከትምህርት/ከድስትርክቱ ፖሊሲ ጋር የሚቃረን ከሆነ፣ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድባቸዋል።. እነዚህ የዲሲፕሊን እርምጃዎች መብቶችን ማጣትን፣ በትምህርት ቤት ዉስጥ መታገድን (ከትምህርት በኋላ፣ ምሳ)፣ ከትምህርት ቤት ውጪ መታገድ እና መባረርን ሊያካትቱ ይችላሉ። ተማሪው ከነዚህ የዲሲፕሊን እርምጃዎች ውስጥ አንዱ ሲያጋጥመው፣ የፍትህ ሂደት የማግኘት መብት አላቸው።

**ከትምህርት ቤት ለጊዜው እገዳ**

ከትምህርት ቤት ውጭ እገዳ የተደረገባቸው ተማሪዎች በእገዳው ጊዜ በማንኛውም የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ካምፓስ ውስጥ እንዲገኙ አይፈቀድላቸውም.። የታገዱ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በኋላ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በታገዱ ቀናት ላይ መሳተፍ አይችሉም።

የተወሰኑ የኮሎራዶ ሕጎች የመታገድ ምክንያቶችን ይቆጣጠራሉ እና ከወላጆች ጋር ይወያያሉ። ከእገዳ የመልሶ ቅበላ ኮንፈረንስ ተማሪውን፣ ወላጁን፣ ዲንን፣ እና የልዩ ትምህርት ጉዳይ አስተዳዳሪን (የሚመለከተው ከሆነ) ያካትታል።.የዚህ ኮንፈረንስ አላማ የባህሪ መደጋገም እና ተጨማሪ የማስተማሪያ ጊዜን ማጣትን ለማስወገድ ስልቶችን ማቀድ ነው።. በዚያን ጊዜ የባህሪ ማሻሻያ ውል ሊፈጠር ይችላል። ተማሪዎች የትምህርት ቤት ስራቸዉን እንዲሰሩ ይጠበቃሉ እና ለዚያ ስራ ዉጤት ሊያገኙ ይችላሉ.

**የትምህርት ቤት ኦፊሰር/ፖሊስ**

Prairie ደህንነቱ የተጠበቀ እና ሰላማዊ የመማሪያ አካባቢን ለመጠበቅ ከአካባቢ ባለስልጣናት ጋር በቅርበት ይሰራል ። የኦሮራ ፖሊስ ዲፓርትመንት የትምህርት ቤት ሰራተኞቻችንን በህጋዊ ጉዳዮች፣ ቅሬታዎች፣ ጥያቄዎች፣ እንድረዱ የትምህርት ቤት ፖሊስን (SRO )ለትምህርት ቤት ይመድባል. የትምህርት ቤት አፊሰር ያው ሃሴት ማለት ነው ። ባለሥልጣኑ በትምህርት ቤት ደኅንነት እና ወንጀል መከላከል ላይ ከመርዳት በተጨማሪ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች ሃሴት ነው።

**የአለባበስ ስርዓት**

የCCSD መካከለኛ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ለትምህርት አካባቢ ምቹ እና ተስማሚ ልብስ እንዲለብሱ የሚበረታታበት አወንታዊ የአለባበስ ስርአት ያስተዋውቃሉ።

የCCSD ፖሊሲ JICAB ተማሪዎች ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ አማራጮች ተገቢውን አለባባስ እንዲለማማዱ ለመርዳት የታሰበ ነው፡፤ ዘር፣ ጾታ፣ የፆታ ማንነት፣ የፆታ አገላለጽ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ኃሳ፣ ሃይማኖት፣ የባህል አከባበር፣ የቤተሰብ ገቢ ወይም የአካል አይነት/መጠን ሳይለይ ሁሉም ተማሪዎች በእኩልነት እንዲስተናገዱ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።.አልባሳት፣ ጌጣጌጦች፣ እቃዎች ወይም የሰውነት ማስጌጫዎች የሚከተሉትን **መሆን አይችሉም፡-**

- ጸያፍ፣ አስቀያሚ ፣ ሴሰኛ፣ ስሜት ቀስቃሽ፣ ስም አጥፊ፣ ወይም ባለጌ
- የጌንግ ቡድን ተሳትፎን የሚያመለክት ።
- የአደንዛዥ ዕፅ፣ ትምባሆ፣ አልኮል ወይም የጦር መሳሪያ አጠቃቀምን የሚያበረታታ
- ማንኛውንም ግለሰብ ወይም ቡድን ማስፈራራት ወይም ማስጨነቅ
- የተወሰኑ የሰውነት ክፍሎችን ማጋለጥ (ማለትም የጾታ ማረቢያ፣ መቀመጫዎች፣ ሆድ እና የደረት አካባቢ)
- የትምህርት አካባቢን ማሰናከል/መረበሽ
- በተማሪው የስነምግባር ህግ የተከለከለ ማንኛውንም ተግባር ማስተዋወቅ
- : ተጨማሪ የአለባባስ/የልብስ መመሪያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:
- አልባሳት ሁል ጊዜ ሁሉንም የውስጥ ልብሶች ለመደበቅ በቂ መሆን አለባቸው (የውስጥ ልብሶች በባህላዊው ውጫዊ ልብስ ስር የሚለበሱ ልብሶች ናቸው)።
- ጫማዎች ሁል ጊዜ መደረግ አለባቸው።
- አደገኛ ተብለው የሚታሰቡ ወይም እንደ መሳሪያ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ጌጣጌጦች በትምህርት ቤት ላይለብሱ ይችላሉ።
- . ፊትን ወይም ጆሮን የሚያደበዝዝ /የሚደብቅ ነገር (እንደ ሀይማኖታዊ ወይም የፊት መሸፈኛ ካልሆነ በስተቀር) በትምህርት ቤት ሊለበሱ አይችሉም።

አልባሳት ወይም ጌጣጌጦች አግባብነት የሌላቸው፣ የሚረብሹ ወይም ከተጠበቀው ውጭ ከሆኑ ተማሪዎች እንዲለውጡ ይጠየቃሉ፤ ለወላጆች ይነገራል እና/ወይም ሌላ የዲሲፕሊን መዘዞች ሊከሰቱ ይችላሉ።

**የተማሪ የገንዘብ ቅጣቶች**

ኮምፒውተሮች፣ መጽሃፎች፣ የክፍል እቃዎች፣ የላብራቶሪ እቃዎች፣ መቆለፊያዎች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ የአትሌቲክስ ዩኒፎርሞች ወይም ቴክኖሎጂን ጨምሮ ከትምህርት ቤቱ የተዋሱትን ማናቸውንም የማስተማሪያ ቁሳቁስ ወይም መሳሪያ ለመጠገን ወይም ለመተካት ተማሪዎች መክፈል ይጠበቅባቸዋል።

**ኮምፒውተር**

እያንዳንዱ ተማሪ ለትምህርት አገልግሎት የሚውል የዲስትሪክት ላፕቶፕ ተሰጥቶታል።.. ይህ ኮምፒውተር ቀኑን ሙሉ ከተማሪው ጋር መቆየት አለበት።.ተማሪዎች በየቀኑ ኮምፒውተራቸውን ቻርጅ አድርገው ወደ ትምህርት ቤት በየቀኑ እንዲያመጡ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች ለጠፉ መሳሪያዎች እና በመሳሪያው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ናቸው። ይህ ከተከሰተ, ቅጣቶች በዚሁ መሰረት ይገመገማሉ.

**የተማሪ መታወቂያ ካርዶች**

ተማሪዎች የቤተመጻሕፍት መጽሐፍትን ለመዋስ ፣ የምሳ ክሬዲት ሲስተም እና የትምህርት ቤት አውቶቡሶችን ለመጠቀም የተማሪ መታወቂያ ካርድ ይሰጣቸዋል። የተማሪ መታወቂያዎ ከጠፋብዎ ወደ መዝገብ ያዥው ዘንድ ሄደው አዲስ ለማግኘት 5 ዶላር ሊከፍሉ ይችላሉ።

**የጠፉ እና የተገኘ ዕቃዎች**

የጠፉ እና የተገኙ ዕቃዎች በካፊቴሪያው ውስጥ ይገኛሉ።. እንደ ጌጣጌጥ፣ ኤሌክትሮኒክስ እና መነጽሮች ያሉ ትናንሽ እቃዎች በዲን ቢሮ እና በሴኩሪቲ ዴስክ ውስጥ ተቀምጠዋል።. ያልተጠየቁ እቃዎች በየወሩ ለበጎ አድራጎት ይለገሳሉ።

**የተማሪ ስጋቶች፣ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች**

. የCCSD የትምህርት ቦርድ፣ አስተዳደር እና ሰራተኞች የሌሎችን መብት በማይጥስ መልክ የተማሪዎችን የመጠየቅ መብቶች እና አሳሳቢ ጉዳዮችን በነባር የግንኙነት ሂደቶች የመግለጽ መብቶችን ያከብራሉ።. ስለሆነም ተማሪዎች አሳሳቢ ጉዳዮችን ለመምህራን እና አስተዳደር ለማስተላለፍ በቂ እድል ሊኖራቸው ይገባል እና እነዚህን ጉዳዮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመወያየት ሰፊ እድል ይኖራቸዋል።

[የ6ተኛ ክፍል የክስተት ሪፖርት]
[የ7ተና ክፍል የክስተት ርፖርት]
[የ8ተኛ ክፍል የክስተት ርፖርት]

**የካፌቴሪያ መረጃ**

የተማሪ ምሳ ሰአት 30 ደቂቃ ነው።.ተማሪዎች ከካፊቴሪያው ምሳ መግዛት ወይም ምሳ ከቤት ይዘው መምጣት ይችላሉ። ቁርስ በየትምህርት ቤቱ ከቀኑ 8፡00-8፡40 በካፊቴሪያ ይሰጣል።: የትምህርት ቤት የምግብ ዋጋ፣ ሜኑ እና የአመጋገብ መመሪያዎችን ለማግኘት፣ ለነጻ ወይም ለቅናሽ ዋጋ ምግብ ለማመልከት፣ ወይም በካፍቴሪያ አካውንት ውስጥ ገንዘብ ለማስቀመጥ፣ እባክዎን ወደ የተማሪ የአመጋገብ አገልግሎት ድህረ ገጽ ይሂዱ፡ http://ccsdcafe.org . ተማሪዎች ለካፊቴሪያ መለያ መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸዋል፣ እና ለዕለታዊ አገልግሎት ገንዘብ በሂሳቡ ውስጥ ሊያቆዩ ይችላሉ።. . ተማሪዎች የምሳ አካዉንታቸዉን መከታተል እና ዝቅተኛ በሚሆንበት ጊዜ መሙላት አለባቸው። ተማሪዎች የመለያ ቁጥራቸውን( PIN )ለሌሎች ተማሪዎች መስጠት የለባቸውም ።. ተማሪዎች በጥሬ ገንዘብ ለምግብ መክፈል ይችላሉ።

**የካፌቴሪያ ደንቦች**

በፕራይሪ በምግብ ሰዓት ተማሪዎች፡-

1. ምግባቸውን በካፊቴሪያ ውስጥ ብቻ መብላት ይችላሉ. ምግብ ወደ ውጭ መዉሰድ አይፈቀድም
2. የበሉበትን ጠረጴዛ ያጸዳሉ እና ቆሻሻቸውን መጣላቸዉን ያረጋግጣሉ።.
3. በምግብ ወቅት በስርአት ተቀምጠው ምግባቸዉን ይመገባሉ እስከሚሰናበቱ ድረስ።.
4. ተገቢውን ቴክኖሎጂ ወደ ካፊቴሪያው ሊያመጡ ይችላል። የቴክኖሎጂ ተገቢ አጠቃቀም የትምህርት ቤት ህጎችን ይከተላል።
5. ከካፊቴሪያ ለመውጣት ከመምህራቸው ፈቃድ ሳያገኙ በቁርስም ሆነ በምሳ ወደ ትምህርት አዳራሾች አይግቡ።
6. በልተው ሲጨርሱ አካባቢያቸውን ያፀዳሉ እና ለመዉጣት እስኪፈቀድላቸው ድረስ ይጠብቃሉ .

7. ተማሪዎች ምሳ በውጭ አቅራቢዎች እንዲቀርብ ማዘዝ አይችሉም።

በእረፍት ጊዜ፣ ተማሪዎች በተመደበላቸው ቦታዎች ብቻ ላይ ይቆያሉ። ደወሉ ሲደወል ተማሪዎች በሰሜን/ጂም አካባቢ በሮች በኩል ወደ ህንጻው እንደገና ይገባሉ። በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ቀናት (ዝናብ፣ በረዶ ወይም ከመጠን በላይ ቅዝቃዜ ) ተማሪዎች በህንፃው ውስጥ ይቆያሉ።

## ላይብረሪ

በቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ ሁሉም ቤተ-መጻሕፍት በኦንላይን ላይ ካታሎግ ሥርዓት ጋር የተገናኙ ናቸው። ተማሪዎች ከቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ መጽሃፍትን መበደር ይችላሉ። ቤተ መፃህፍቱ ለተማሪው ወቅታዊ የኢንተርኔት መጠቀም ፍቃድ ካላቸው ኮምፒዩተሮችም አሉት።በትምህርት ቀን፣ የምሳ ሰአትን ጨምሮ፣ ተማሪዎች ቤተ መፃህፍቱን መጠቀም የሚችሉት በአስተማሪያቸው የተፈረመ የይለፍ ወረቀት ካላቸው ብቻ ነው። ከቤተ-መጽሐፍት መጽሃፍትን እና ሌሎች ነገሮችን በሚበደሩበት ጊዜ ተማሪዎች የፕራይሪ የፎቶ መታወቂያ/ላይብረሪ ካርዳቸውን ማሳየት አለባቸው።

## የምክር አገልግሎት

የትምህርት ቤት አማካሪዎች በአካዳሚክ፣ በግላዊ/ማህበራዊ እና በኮሌጅ/በሙያ ጉዳዮች ላይ ሊረዱ ይችላሉ። ተማሪዎች ከአማካሪያቸው ጋር በመምህራቸው፣ በአስተዳዳሪያቸው ወይም በወላጆቻቸው ጥያቄ ወይም ሪፈራል መገናኘት ይችላሉ።

### የስኬጁል ማስተካካያ

የስኬጁል ማስተካካያ የሚካሄደው የተማሪዎችን አካዴሚያዊ ወይም የህክምና ፍላጎቶችን ለመደገፍ ሲሆን በክፍሉ ውስጥ ያለው ቦታ ሲፈቅድ ብቻ ነው።. ማስተካካያዎች የሚከናወኑት በሩብ ዓመቱ የመጀመሪያ ሳምንት ውስጥ ብቻ ነው እና ዋስትና አይሰጡም።

## የPRAIRIE መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእጅ ስልክ *መመሪያ*

## የPRAIRIE መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእጅ ስልክ *መመሪያ*

ተማሪዎች የሞባይል ስልኮቻቸውን ከትምህርት ቤት በፊት፣ በምሳ ሰአት እና ከትምህርት በኋላ ብቻ እንዲጠቀሙ ይፈቀድላቸዋል። የተማሪ ስልኮች ቀኑን ሙሉ በኪሳቸው ወይም በቦርሳቸው ውስጥ መቆየት አለባቸው። የተማሪ ስልክ ከታየ፣ እባኮትን "የቴክኖሎጂ ቅጣቶች " ከታች ያለውን ግራፍ ይመልከቱ።በትምህርት ቤቱ ህንፃ ውስጥ ተማሪዎች ሽቦ አልባ የጆሮ ማዳመጫዎችን መጠቀም አይፈቀድላቸውም። አንድ አስተማሪ ተማሪዎች በክፍል ጊዜ ሙዚቃ እንዲያዳምጡ ከፈቀደ፣ በባለገመድ የጆሮ ማዳመጫዎች እና በተማሪው ኮምፒውተር ብቻ ይሆናል።

### የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ መሳሪያዎች (ECD)

ተማሪዎች ሁሉንም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መሳሪያዎችን (ኢ.ሲ.ዲ.) በትምህርታዊ ሁኔታ እና በሚመለከተው የ CCSD የቦርድ ፖሊሲዎች JICJ እና JS መሰረት መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በስነምግባር እና በኃላፊነት የመጠቀም ሃላፊነት አለባቸው።.የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች በኃላፊነት እና በአክብሮት ጥቅም ላይ እስከዋሉ ድረስ ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በምሳ ሰአት በካፌቴሪያ ውስጥ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።. . ተማሪዎች መሳሪያዎቻቸውን በማንኛውም ጊዜ ለመጠበቅ ሃላፊነቱን ይወስዳሉ ።. ወደ ትምህርት ቤት ለመጣው የግል ንብረት መጥፋት ትምህርት ቤቱ እና ድስትርክቱ ተጠያቂ አይደሉም።

### ስልኮች

ሁሉም ተማሪዎች በፈቃድ የትምህርት ቤት ስልኮችን መጠቀም ይችላሉ . እነዚህ በቢሮዎች ውስጥ ይገኛሉ.

### የተማሪ እሜይል

እያንዳንዱ ተማሪ የ Outlook® ኢሜይል መለያ ተሰጥቶታል። ከትምህርት ቤት ጋር ለተያያዙ ስራዎች ጥቅም ላይ እንዲውል የታሰበ ነው።. እያንዳንዱ መምህር የ Outlook ኢሜይል መለያም አለው።. እነዚህ የግል ኢሜይል መለያዎች አይደሉም እና ሁሉም ይዘቶች በት/ቤት እና በዲስትሪክት ፖሊሲዎች የሚተዳደሩ ናቸው።

### የኤሌክትሮኒክስ *ሥነ-ምግባር*

የኤሌክትሮኒክስ መረጃ በቀላሉ ሊገለበጥና ሊባዛ ስለሚችል፣ በተለይ በኮምፒዩተር አካባቢ የሌሎችን ሥራ እና የግል መግለጫ ማክበር አስፈላጊ ነው። የስልጣን ታማኝነትን መጣስ፣ ክህደትን፣ ግላዊነትን ህግ መጣስ ፣ ያልተፈቀደ አገባብ እና የቅጂ መብት መጣስ ለህጋዊ እርምጃ ምክንያቶች ናቸው።

### የተማሪ ላፕቶፖች እና የገመድ አልባ ግንኙነት

ተማሪዎች የየራሳቸውን የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መሳሪያዎችን በመጠቀም የዲስትሪክቱን ሽቦ አልባ አውታር በት/ቤት ማግኘት ይችላሉ. የዲስትሪክቱን ሽቦ አልባ አውታር የማግኘት ፍቃድ በምንም መልኩ ወላጆች ለተማሪዎቻቸው ኢሲዲ እንዲያቀርቡ አያስገድድም። የዲስትሪክቱ ሽቦ አልባ አውታር መዳረሻ ለአካዳሚክ መተግበሪያዎች እና እንቅስቃሴዎች ተፈቅዷል።

በ CCSD የቦርድ ፖሊሲ JICJ መሰረት የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክትም ሆነ የፕራይሪ መለስተኛ ደረጃ ት/ቤት ለተበላሹ፣ ለተሰወሩ ወይም ለተሰረቁ የተማሪ ግላዊ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መሳሪያዎች ተጠያቂ አይደሉም። የዲስትሪክቱም ሆነ የፕራይሪ መለስተኛ ደረጃ ት/ቤት ከማገነኘት ባለፈ የECD ጥገና ወይም የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት አይችሉም።

### ተቀባይነት ያለው የኢሲዲ ገመድ አልባ ማግኛ መመሪያዎች

የበይነመረብ ተደራሽነት ለትምህርት አካባቢ አግባብ ያልሆኑ ጣቢያዎችን ለመዝጋት በተዘጋጀው የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ማጣሪያ ውስጥ ያልፋል. ተማሪዎች በዲስትሪክቱ ሽቦ አልባ አውታር ከግል የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መሳሪያዎቻቸው ጋር ኢንተርኔት ሲጠቀሙ፣ ሁሉንም የዲስትሪክት የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን፣ እንዲሁም የዲስትሪክቱን የበይነመረብ ተቀባይነት ያለው የአጠቃቀም ስምምነት ውሎች እና ሁኔታዎች መከተል ይጠበቅባቸዋል።. የተማሪው ተገቢ ያልሆነ የግላዊ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መሳሪያ አጠቃቀም በሚመለከተው የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ እና/ወይም ህግ መሰረት መዘዞችን ያስከትላል።

## የጤና አገልግሎቶች

### ህመሞች እና አደጋዎች

በትምህርት ቀን ነርስ በሥራ ላይ ነው።. . የጤና ክሊኒካችን የሚገኘው በተማሪዎች አገልግሎት ቢሮ ነው። ድንገተኛ ካልሆነ በስተቀር፣ ተማሪዎች ወደ ጤና ክሊኒክ ለመግባት ከመምህራቸው ፈቃድ ማግኘት አለባቸው. ነርሷ የተማሪውን የጤና ስጋት ምንነት ይገመግማል እና ተማሪው ወደ ቤት መሄድ ወይም ህክምና ለማግኘት ወደ ሃኪም ቤት መወሰድ አስፈላጊ መሆኑን ለማወቅ ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል። ተማሪዎች በትምህርት ቤት ሲታመሙ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎችን ለማግኘት እና ወደ ቤት ለመሄድ በጤና ክሊኒክ በኩል መሄድ አለባቸው።

### *መድሃኒት*

1. በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች ወደ ጤና ክሊኒኩ በዋናው ኮንቴይነር ከመጡ ብቻ "በትምህርት ቤት የሐኪም ማዘዣ/የሆሚዮፓቲክ መድኃኒት የመስጠት ፍቃድ" ፎርም ጋር ከተወሰደ ብቻ ነው።. ይህ ቅጽ በጤና ክሊኒክ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በሁለቱም የተማሪው ሐኪም እና በወላጅ/አሳዳጊ መፈረም አለበት።
2. አንድ ተማሪ በት/ቤት አልፎ አልፎ ያለ ሃኪም ማዘዣ የማስተጋሻ መድሃኒት ከፈለገ፣እንደ Tylenol ያሉትን ተማሪው የ OTC መድሃኒት በጤና ክሊኒክ ውስጥ ማግኘት ይችላል; በጤና ክሊኒክ ውስጥ ለተማሪዎች የማስተጋሻ መድሃኒት

ከመሰጠቱ በፍት " አልፎአልፎ የማስተጋሻ መድሃኒት ለልጄ ይሰጥ የሚል " ቅጽ በወላጅ/አሳዳጊ በኦንላይን ላይ መሞላት አለበት።

3. አስም እና/ወይም ለሕይወት አስጊ የሆነ አለርጂ ካለባቸው ተማሪዎች በስተቀር ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ ምንም አይነት መድሃኒት እንዲወስዱ አይፈቀድላቸውም።ተማሪው፣ ሀኪሙ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የትምህርት ቤቱ ነርስ ተማሪው በኃላፊነት ስሜት እንዲሰራ ከተስማሙ አስም እና/ወይም ህይወትን የሚያሰጋ አለርጂ ያለባቸው ተማሪዎች መድሃኒቱን
4. እራሳቸው እንዲወስዱ ተፈቅዶላቸዋል። ያለበለዚያ አስም እና/ወይም ለሕይወት አስጊ የሆነ የአለርጂ መድሐኒት ከተማሪው ሐኪም ተገቢው የህክምና ሰነድ በጤና ክሊኒክ ውስጥ ማስቀመጥ ይቻላል።.

**የትምህርት ቤት የክትባት ህግ (CCSD ፖሊሲ JKD-1-E-#9)**

የኮሎራዶ ትምህርት ቤት የክትባት ህግ ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ለመግባት የክትባት ህጉን ማክበር አለባቸው። ይህን ህግ የማያከብሩ ተማሪዎች ወደ ክፍል እንዳይገቡ ሊከለከሉ ይችላሉ። ወቅታዊ የክትባት ግልባጭ በእያንዳንዱ ተማሪ የትምህርት ቤት የጤና ፋይል ውስጥ ተከማችቷል። በሕክምና ምክንያት ከክትባት ነፃ መሆን ካስፈለገ በሃኪም መፈረም እና ቀኑ መመዝገብ አለበት. ተማሪው በግል ወይም በሀይማኖት ምክንያት ከክትባት ነፃ መሆን ካስፈለገ ፣ ፎርሙ በየትምህርት ዓመቱ በወላጅ/አሳዳጊ መፈረም እና ቀኑ መጻፍ አለበት። እባኮትን ከጤና ጋር የተገናኙ ጥያቄዎችን/ስጋቶችን በተመለከተ የጤና ክሊኒኩን ለማነጋገር ነፃነት ይሰማዎ፡ ስልክ፡ 720-747-3016፡ ፋክስ፡ 720-747-3185።

**የሴፍ ቱ ቴል(Safe-2-Tell ) -*ሪፖርት ማድረጊያ***

. Safe-2-Tell እርስዎን፣ ጓደኞችዎን፣ ቤተሰብዎን ወይም ማህበረሰብዎን የሚመለከት ወይም የሚያስፈራራ ማንኛውንም ነገር በምስጥር ሪፖርት የማድረጊያ መንገድ ነው። Safe-2-Tell የሚንቀሳቀሰው በኮሎራዶ ስቴት ፓትሮል ነው።




**ጥያቄዎች/ ማንን እንደሚያነገሩ መረጃ**

**ዋና ቁጥር 720-747-3000**
**የ6ተኛ ክፍል ቢሮ 720-747-3066**
**የ7ተኛ ክፍል ቢሮ 720-747-3030**
**የ8ተኛ ክፍል ቢሮ 720-747-3040**
**የአቴንዳንስ ቢሮ 720-747-3010**
**ክሊኒክ /የነርስ ቢሮ720-747-3016**


# Technology Consequences

**1st violation**





Devices are placed in a **locked bag** in the **grade level office** until **3:45**. Parents/guardians are **contacted**.

**2nd violation**





Student receives all **step 1 consequences** **AND** student receives a **referral** and dean **consequence**.

**3rd violation**




Student receives all **step 2 consequences** **AND** parent/guardian **meeting** with dean required.

**4th violation**





Student receives all **step 2 consequences** **AND** **each following day** devices are placed in a **locked bag** in the grade level office before school and **remain there** until after school.

## Drug Policy



The school nurse can keep and dispense some over the counter and prescription medications with parent/guardian permission. Students may carry medication or inhalers only if approved by the nurse.



Drugs are **not allowed** at school or on campus. Possessing, sharing, selling, buying, and/or using drugs on campus can result in suspension or expulsion. Prohibited drugs include:

- **Cigarettes**
- **Vapes**
- **Marijuana**
- **Alcohol**
- **All other drugs & medications**



## Weapons Policy

Weapons are **not allowed** at school or on campus. Possessing weapons on campus can result in suspension or expulsion. Prohibited weapons include:

- **Guns**
- **Knives**
- **Pocket knives**
- **Brass Knuckles**
- **Any item intended or used to hurt others**
- **Fake or toy weapons**

